# የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ለሚሰደዱ ዜጎች የበለጠ ድጋፍ እንዲደረግ አሳሰቡ

*አዲስ አበባ, ረቡዕ ጥር 22, 2016*

በሱዳን በተከሰተው አሳሳቢ ግጭት ወደ 8 ሚሊዮን የሚጠጉ ለተፈናቀሉ ዜጎች የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ፊሊፖ ግራንዲ የሰዎችን መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት አስቸኳይና ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግላቸዉ ጠይቀዋል።

ኮሚሽነሩ ለሶስት ቀናት በኢትዮጵያ ባደረጉት ጉብኝት፣ በቅርቡ በሱዳን በተቀሰቀሰዉ ግጭት ምክንያት ወደ ሀገሪቱ የገቡትን የሱዳን ስደተኞችን ለመርዳት የኢትዮጵያ መንግስት በUNHCR እና በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ እያደረገ ያለውን ጥረት ተመልክቷል። ኮሚሽነሩ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወደሚገኘው አሶሳ በማቅናት፣ በአሁኑ ወቅት በኩርሙክ ጊዜያዊ ማቆያ ዉስጥ ከሚገኙ ከ20ሺ በላይ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂቶቹን መካከል ጥቂቶችን አነጋግሯል። ከመጋቢት 2015 ጀምሮ ከ100ሺ በላይ ሰዎች ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል፣ ከነሱም ወደ 47ሺ የሚጠጉ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ናቸዉ። እነዚህም በኢትዮጵያ ቅድሞ ከሚገኙት 50ሺ ሱዳናውያን ስደተኞች በተጨማሪ ናቸዉ።

“ስደተኞቹ የቤተሰብ፣ የጓደኛ፣ የቤት ማጣት አሳዛኝ ታሪኮቻቸዉን አጋርተዉኛል፣ ሆኖም በዚህ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ፣ ድጋፍ እና እድል ከተሰጣቸዉ ወደ ፊት ለመራመድ ያላቸውን ቁርጠኝነትም አይቻለሁ” ኮሚሽነሩ ብለዋል።

ኮሚሽነር ግራንዲ መንግስትንና የአካባቢውን ማህበረሰቦችን ከብዙ ስደተኞች ማስተናገድን ጨምሮ የራሳቸው ተግዳሮቶች ቢያጋጥሟቸውም መሬት በመመደብ እና ለስደትኞች አቀባበል ስላደረጉላቸው አድንቀዋል።

"ኢትዮጵያ ከሱዳን ለመጡት የተፈናቀሉ ዜጎች የምታደርገው ልግስና የሚያስመሰግን በመሆኑ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የላቀ ድጋፍ ሊደረግላት ይገባል። ለጋሽ ሃገሮች ተጨማሪ ድጋፍ ካላደረጉ ለተረጂዎች መድረስ እጅግ በጣም ከባድ ይሆናል” ሲል ግራንዲ ጥሪ አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያ ከሱዳን የሚሰደዱ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን እየተቀበሉ ካሉት ጎረቤት ሀገራት መካከል አንዷ ነች። ባለፈው ሳምንት ወደ ቻድ የገቡት አዲስ ስደተኞች ቁጥር ካለፈው ሚያዚያ ወር አንስቶ 500ሺ በላይ መድረሱ እና በደቡብ ሱዳን አማካይ 1.5ሺ ሰዎች በየቀኑ ወደ ሀገሪቱ እየተሰደዱ ናቸዉ።

ለአዲስ መጪዎች ጥበቃና ይህይወት አድን አገልግሎቶች ለማድረስ፣ UNHCR፣ የኢትዮጵያ መንግስትን በስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ደርጅት (RRS) አመካኝነት፣ የክልልና የአካባቢ ባለስልጣናትን ጨምሮ ድጋፍ እያደረገ ነው።

አዲስ የገቡ ሱዳናውያን ስደተኞች ከድንበር አከባቢዎች ርቀው ወደ ተዘጋጀላቸኡ አዲስ የመጠለያ ጣቢያዎች እየተዘዋወሩ ይገኛሉ። መንግስት፣ UNHCR እና ሌሎች አጋር የግብረ ሰናይ ደርጅቶች ፣ ስደተኞች በአገሪቷ በሚሰጡ መሰረታቂ አገልግሎቶች ዉስጥ እንዲካተቱ በመስራት ላይ ናቸዉ። እነዚህ መሰረታዊ አገልግሎቶች (ትምህርት፣ ጤናና የንፁህ ውሃ አቅርቦት) ተጠናክረው ስደተኞቹንና እነርሱን የተቀበሉት ማህበረሰቦች ትጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሰራ ነዉ።

ከፍተኛ ኮሚሽነሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ሌሎች በርካታ ክልሎች ድጋፍ እንደሚያስፈሊጋቸዉ አስምረዋል። እነሱም ሶማሌ ክልል ከላሳኖድ ሶማሊያ የመጡ የስደተኞች መጉረፍ፣ በአየር ንብረት መዛባት የተፈጠረዉ ደርቅ ውጤቶችና የቅርብ ጊዜ የተከሰተዉ የሶማሌ ክልል ጎርፍን ያካትታል። በተጨማሪም የገንዘብ ድጎማ እየቀነሰ በመሄዱ በሰብአዊ ምላሽ ላይ በተለይም በጤናና በትምህርት ላይ ያለውን ተጽእኖ አመልክቷል።

ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ከሚባሉት ስደተኞችና ተፈናቃዮችን ከሚቀበሉት ሃገራት መካከል አንዷ ናት። በአፍሪካ ሶስተኛዋ ትልቁ የስደተኞች አስተናጋጅ ሀገር በመሆኗ፣ በአሁኑ ወቅት ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞችን ያቀፈች ስተሆን በተለይም ከደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ኤርትራና ሱዳን የተወጣጡ ሲሆኑ ወደ 3.5 ሚሊዮን የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥ ተፈናቅለዉ ይገኛሉ።

ባለፈው ዓመት እ.አ.አ 2023 መጨረሻ ላይ፣ የUNHCR Ethiopia መርሃ ግብሮች በዐለም አቀፍ ደረጃ ከተከፈሉት በጣም ያነሰዉ ነበር (ከሚያስፈልገው 431 ሚሊዮን ዶላር 36 በመቶው በቻ ንዖ የተገኘዉ)። እ.አ.አ በ2024 ዐ.ም. አጠቃላይ የUNHCR ኢትዮጵያ የተተለመው በጅት 426 ሚሊዮን ዶላር ደርሷል።

## ለበለጠ መረጃ የሚቀጥሉትን ሰዎች ያነጋግሩ:


- በናይሮቢ (regional), Faith Kasina, kasina@unhcr.org, +254 113 427 094
- በአዲስ አበባ, Lucrezia Vittori, vittori@unhcr.org, + 251 97 810 4031
- በጄኒቫ፣ William Spindler, spindler@unhcr.org; +41 79 549 5998